የሰ/መ/ቁ. 105708

ግንቦት 19 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች**፡- አቶ በፈቃዱ ከበደ- ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ካሊድ መሐመድ - ጠበቃ ገመቹ ጉተማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም እርቅ ማድረጋቸውን ገልጸው ይኼው እርቅ እንዲፈፀምላቸው ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃጸም በማቅረባቸው ምክንያት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም አመልካች ያቀረቡትን የአፈጻጸም ማመልከቻ መነሻ በማድረግ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡበት አድርጎ የአሁኑ ተጠሪ ለመፈጸም የሚቻል ጉዳይ አይደለም፣ሽምግልና እኛ አልመረጥንም የሚሉ ምክንያቶችን አንስተው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም ሽማግሌዎችን ግራ ቀኙ በፍላጎታቸው መርጠው ተጠሪ ለአመልካች ብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ መወሰኑን ገልጸው አፈፃጸሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና በ18/07/06 ዓ/ም ተሰጠ የተባለውን ውሳኔ መርምሮ የእርቅ ውጤቱ ግራ ቀኙ ስለመቀበላቸው በፊርማ ያላረጋገጡት መሆኑን፣ውሳኔው የጥቂት ሽማግሌዎች ውሳኔና ግራ ቀኙ ያልተቀበሉት መሆኑን፣ በመድሃኒት ግምት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣ በሰነዱ ላይ ከተጠቀሱት ሽማግሌዎች ውስጥ ሶስት ሰዎች ያልፈረሙበት በመሆኑ ሽማግሌዎቹ በአንድ ድምጽ ያልወሰኑበት ስለመሆኑ መገንዘብ እንደማያስቸግር ዘርዝሮ ውሳኔውን ለማስፈፀም የሚቻል አይደለም በማለት የአፈፃጸም መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ጉዳዩን ግራ ቀኙ በመረጧቸው ሽማግሌዎች የሚሰጠውን ውሳኔ ለመቀበል ከተጠሪ ጋር በ18/07/2006 ዓ.ም ውል መፈራረማቸውን ተጠሪ ባልካዱበትና በዚሁ ውል መሰረት የተሰየሙት

ሽማግሌዎች ግራ ቀኙን በመስማትና ጉዳዩን በማጣራት ተጠሪ በሽማግሌዎች ፊት 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) ለመክፈል ከመስማማታቸውም በላይ ሽማግሌዎቹ ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ እና የመድሃኒቶች ዋጋም በባለሙያ ተጣርቶ እንዲለይ በማለት ወስነው እያለ ጉዳዩን ከተመለከቱትና ውሳኔ ከሰጡት ሰባት ሽማግሌዎቹ ውስጥ  አምስቱ ፈርመው ሁለቱ ከአከባቢው በመለየታቸው ሳይፈርሙ የቀሩ ሁኖ በውሳኔው ላይ ግራ ቀኙ አልተስማሙም፣ በሽማግሌዎችም ሙሉ በሙሉ አልተፈረመም ተብሎ የሚፈፀም አይደለም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ እንዲዘጋ መደረጉ ያለግባብ ነው የሚለው ነው፡፡ አቤቱታው ተመርመሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎቱም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመለኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ውድቅ የተደረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከግራ ቀኙ አጠቃላይ ክርክር መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ክርክር የተነሳው አመልካች በአዳማ ከተማ ቀበሌ 12 ክልል ውስጥ ከወ/ሮ ትንሳኤ አበበ ላይ ሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ ውል ለሁለት አመት ከተከራዩ በኋላ የንግድ ቤቱን ሳሌም መድኃነት ቤት በሚል ስያሜ የንግድ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ስራቸውን በመስራት ላይ እያሉ የቤቱ አከራይ ለአሁኑ ተጠሪ ቤቱን የሸጡላቸው መሆኑን፣በሽያጭ ውሉ የተከራይ መብት የተጠበቀላቸው ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ከገዙ በኋላ ነሐሴ 07 ቀን 2005 ዓ.ም መድኃኒትና የተለያዩ ንብረቶች እያሉበት የቤቱን ቁልፍ ሰብረው በሌላ ቁልፍ በሩን በመዝጋት በአመልካች ላይ ሁከት መፍጠራቸውን ገልጸው አመልካች በአዳማ ወረዳ  ፍርድ ቤት የሁከት ይወገድልኝና ኪሳራ ይከፈለኝ የሚል ክስ በተጠሪ ላይ አቅርበው እስከ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ተከራክረው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት መልሶት ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ በቀረበው ሃሳብ መሰረት ግራ ቀኙ ሽማግሌዎችን መርጠው፣ ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሳኔ የሚቀበሉ መሆኑን በ18/07/2006 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ተፈራርመው የተመረጡት ሽማግሌዎችም ግራ ቀኙን ከሰሙ በኋላ አመልካች ከአቀረቡት የብር 180,000.00 (አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ) ብር እና ተጠሪ ከአቀረቡት የብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ) መካከል ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ፣እንዲሁም ከመድኃኒት ቤቱ ውስጥ ታሽጎባቸው የተባሉሽና ያልተበላሹ መድኃኒቶች በጤና ጥበቃ ባለሙያ ተለይተው እንዲወጡና የተጎዱና አገልግሎት የማይሰጡ መድኃኒቶች በባለሙያ በሚቀርበው ዋጋና ተመን መሰረት እንዲከፈሉ በሚል ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ከዚህ የግልግል ውሳኔ በኋላም በፍርድ ቤት የተያዘው ክርክር እንዲቋረጥ መደረጉን አመልካች ዘርዝርው የሚከራከሩ መሆኑን፣ ተጠሪ በበኩላቸው በ18/07/2006 ዓ/ም የፈረሙት የሁከት ይወገድልኝ ጉዳይ ላይ በሽምግልና እንዲታይ ለማድረግ እንጂ አሁን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ውሳኔ እንዲሰጥ ያለመሆኑን፣ሽማግሌዎችንም የመረጡበት አግባብ ያለመኖሩን እንዲሁም አከራከሪውን ቤትም ከወ/ሮ ትንሳኤ አበበ የገዙ ያለመሆናቸውንና አጠቃላይ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሰጡ የተባሉት ሽማግሌዎች በአመልካች የተመረጡና ተጠሪ የማያውቋቸው መሆኑን ዘርዝረው በሕግ አግባብ የተሰጠና የተወሰነ የሽምግልና ውሳኔ ስለሌለ ሊፈጸም የሚችል አይደለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

ከግራ ቀኙ የክርክር ይዘትና በ18/07/2006 ዓ.ም ተሰጠ ከተባለው የውሳኔ ይዘት ለመገንዘብ የተቻለው ጉዳዩ የታየው በቤተዘመድ የሽምግልና ዘዴ መሆኑን፣ ይህ ስርዓት ደግሞ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን ለ3ኛ ወገን አቅርበው የግልግል ዳኛው የሚሰጠውን ውሣኔ የሚቀበሉበት መንገድ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 3325 - 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎችና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315 - 319 እና 350 - 357 የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ስለዚሁ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ አደራረግና አፈፃፀም የሚገዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ በሕጉ አግባብ የተደረጉ የቤተዘመድ የሽምግልና ስምምነቶች ሊፈፀሙ የሚችሉ ስለመሆኑ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 3325 - 3346 ድረስ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለይ ሲታዩም የግልግል ስምምነቶች እንደልዩ ውሎች ሊታዩ የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ስለቤተዘመድ የሽምግልና ግልግል ትርጉም የሚያስቀምጠው የፍ/ሕ/ቁ. 3325 ግልግል ውል ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ውል ግዴታዎች የሚቋቋሙበት፣ የሚለወጡበት ወይም ቀሪ የሚሆኑበት ስምምነት እንደመሆኑ መጠን ውል ስለመኖሩ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች /elements/ በቤተዘመድ የግልግል ስምምነትም /arbitral submission/ ተሟልተው ሊገኙ ይገባል፡፡ በመሆኑም የግራ ቀኙ ወገኖች ችሎታ፣ የግልግሉ ጉዳይ ሕጋዊነት እና በሕጉ የሚፈለግ ከሆነ ፎርም ተሟልተው መገኘት የቤተዘመድ ግልግሉን ስምምነት መኖሩን የምናረጋግጥባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለሆነም በቤተዘመድ የግልግል የሽምግልና ዘዴ ቅድመ ሁኔታው ግራ ቀኙ በሕጉ ፊት የሚፀና /valid/ የግልግል ስምምነት ገብተው መገኘት ነው፡፡

በሕጉ አግባብ በተደረገ የግልግል ስምምነት መሠረት የግራ ቀኙን ጉዳይ ክርክር የግልግል ዳኛ መመልከት ከጀመረ በኋላ ሊከተል የሚገባውን ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ.3345 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317/1/ ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ የግልግል ዳኛ ክርክሩን መምራት ያለበት በተቻለ መጠን የመደበኛ ዳኝነት አካሄድን ተከትሎ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች የመስማት፣ ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብና የመጠየቅ መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ እና የዳኝነት አሠጣጥም በዚህ ረገድ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ሊከተል የሚገባው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ይሁን እንጂ የግልግል ዳኛ የዳኝነት አካሄድ የመደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድን መከተል ያለበት ቢሆንም እንደ መደበኛ ፍ/ቤት የዳኝነት አካሄድ እጅጉን የጠበቀ እንዲሆን የማይጠበቅ መሆኑን የተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ያስረዳል፡፡ የቤተዘመድ የግልግል ዳኞች የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318 ስር የተመለከተ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት ስር ውሳኔው በድምጽ ብልጫ እንደሚሰጥ ተቀምጧል፡፡ የግልግል ወይም የቤተዘመድ ዳኛ የሚሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 350 እና ተከታዮቹ መሠረት በበላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ እስካልተለወጠ ድረስ በመደበኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በሚፈፀምበት ሥርዓት ቀርቦ ሊፈፀም የሚችል መሆኑንም የፍ/ሕ/ቁ. 3345/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በግልግል ዳኛ የሚሰጥ ውሣኔ የመጨረሻ ነው የግልግል ውሉም ውል እንደመሆኑ መጠን በአግባቡ እስከተቋቋመ ድረስ ተዋዋይ ወገኖችን የሕግን ያህል የሚያስገድድ፣ በቃላቸው እንዲታሠሩ የሚያደርግ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 3325 'ን' ከፍ/ሕ/ቁ. 1731 ጋር አጣምረን ስንመለከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በ18/07/2006 ዓ.ም የተደረገውን ስምምነት መፈረማቸውን ሳይክዱ፣ ይህ ስምምነት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ጋር የተያያዘ እንጂ አሁን ክርክር ያስነሳውን ውሳኔ በቤተዘመድ ሽምግልና ለማሳየት

የተደገረ አይደለም፣በዚህ ረገድ የግልግል ውል አላደረግኩም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሌለና በግልጽ ያልተካደ ስለመሆኑና ይኸው ውል ስለመኖሩ የበታች ፍ/ቤትም ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ የግልግል ውሉ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ስለመደረጉና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሣውን አለመግባባት ለማስታረቅ ጉባዔዉ መቋቋሙን፣ ጉባዔው ያየውንና የወሰነውን ለመቀበል ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበት እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖችና ሽማግሌዎቹ ፊርማቸውን ያኖሩበት ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ከዚህ ስምምነት በኋላ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠው የግልግል ዳኞች ውሣኔም መሠረት ያደረገው ይህንኑ ውል ሁኖ ስለጉዳቱ መጠን ግራ ቀኙን ተዋዋይ ወገኖች በማስተማመንና በማጣራት የተዋዋይ ወገኖች ሀሳብ ከቀረበ በኋላ በአመልካች ላይ የደረሰ የጉዳት መጠን በሽማግሌዎች ተለይቶ የተወሰነ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገውን ስምምነትና የውሳኔ ሰነድ በፍርድ ባለእዳ በሆኑት ተጠሪ በኩል የተቆጠሩት ሽማግሌዎች መደገፋቸውን ጭምር በትዕዛዙ ሶስተኛ መስመር ላይ ከአሰፈረው በኋላ አመልካችና ተጠሪ በሽማግሌዎች የውሳኔ ሰነድ ላይ በፊርማ አላረጋገጡም በማለት ያስቀመጠው ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በቅድመ ሁኔታነት የማያስቀምጡትን ጉዳይ በመሆኑ ሕጋዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ከፍ/ሕ/ቁ. 3318-3324 ስር በተመለከቱት የሚገዛ ሣይሆን ከፍ/ሕ/ቁ. 3325-3346 ባሉት ድንጋጌዎች የሚገዛ ስለመሆኑ በ18/07/2006 ዓ.ም የተደረገው የግልግል ውል ይዘቱ ያሣያልና፡፡ ሰባት ዳኞች ተሰይመው በዚህ ቀን ውሣኔ የተሰጠውም ተዋዋይ ወገኖችን በማስተማመንና ተገቢው ማጣራት ተደርጎ መሆኑ የግልግል ዳኝነት በጥብቅ የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ሥርዓት እንዲከተል ሕጉ የማይጠብቅ መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 317 ከተመለከተው ድንጋጌ አኳያ ተዳምሮ ሲታይ ጉዳዩ በቤተዘመድ የግልግል /arbitration/ አልታየም ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ከዳኞቹ ውስጥ ሁለቱ ያለመፈረማቸውም ውሳኔው በድምጽ ብልጫ የተሠጠና አብላጫ ድምጽ የፈረመበት በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 318(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ውሳኔውን አልተሰጠም ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም የሽምግልና ዳኞች ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍሉትን የገንዘብ መጠን ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) መሆኑን ከአስቀመጡ በኋላ ቤቱ ውስጥ ታሽጎባቸው የተባለሹና ያልተበላሹ መድኃኒቶ በባለሙያ በሚቀርበው ዋጋና ተመን መሰረት እንዲከፍሉ በማለት ወስነው እያለ የስር ፍርድ ቤት ግምታቸው ሳይታወቅ እንደመጨረሻ ውሳኔ የሚታይ አይደለም በማለት ያሰፈረው ምክንያትም በባለሙያ እንደሚገመት መገለፁ ግምቱ የሚታወቅ መሆኑ የሚያሳይ እንጂ ግምቱ አልታወቀም ሊያስብል የሚችል ባለመሆኑ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በመጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገው የግልግል ውል ሠነድ ላይ ግራ ቀኙ የሚመርጧቸው ሽማግሌዎች የሚወስኑትን እንደሚቀበሉ መስማማታቸውና ውሣኔ የማሣለፍ ሥልጣኑም ለሽማግሌዎች የሰጡ መሆናቸው ተገልፆ እያለ የስር ፍ/ቤት ሕጋዊ የቤተዘመድ ሽምግልና ውሳኔ የለም በማለት ተጠሪ በሽማግሌዎቹ የተወሰነውን ገንዘብ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገደዱም ሲል የሰጠው ውሣኔ በፍ/ሕ/ቁ. 3325- 3346 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315-319 እንዲሁም ከቁጥር 350-357 ድረስ የተመለከቱትን ለማስረጃነት ከቀረበው ሰነድ ይዘት ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18118 ሚያዚያ 17 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 282882 ሰኔ 06 ቀን 2006 ዓ/ም፣ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 186600 መስከረም 07 ቀን 2007 ዓ/ም የጸናው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በ18/07/2006 ዓ/ም በሽማግሌዎቹ የተሰጠው ውሳኔ የሚፈጸም ነው በማለት ውስነናል፡፡ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ገንዘቡን እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይገባል ብለናል፡፡
3. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔውን እንዲያስፈጽም ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

## የ ሀ ሳ ብ ል ዩ ነ ት

እኔ በተራ ቁጥር ሁለት ስሜ የተገለፀው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው ውሳኔ የማልስማማ በመሆኑ፣ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡ ከስራ ባልደረቦቼ በሀሳብ የተለየሁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 18118 ሚያዝያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም በሳፈረው የፍርድ ባለመብት ሆነው ስማቸው በተሰየመው አመልካችና የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ በተሰየመው ተጠሪ መካከል በአፈፃፀም የተደረገ የቃል ክርክር ተጠሪ የግልግል ዳኞችን ያልመረጥን ስለሆነ የግልግል ዳኞች ውሳኔ ነው ተብሎ የመጣውን የሽማግሌዎች ውሳኔ የመፈፀም ግዴታ የለብኝም የሚል ክርክር የቀረበ መሆኑን ከግልባጩ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ አመልካች ባቀረበው የአፈፃፀም ክስ፣ ተጠሪ ምን አይነት መልስ በፅሁፍ እንደሰጠ የሚገልፅ አይደለም፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪ የሚላቸውን ጭብጦች በጥያቄ መልክ ካስቀመጠ በኋላ ግራ ቀኙ የተስማሙበት የዕርቅ ውጤት በድጋሚ ሽማግሌዎች ወስነውና ግራ ቀኙን አስማምተው ካላቀረቡ በስተቀር አሁን ያቀረበውን የእርቅ ውጤት ማስፈፀም እንደማይችል ገልፆ መዝገቡን የዘጋው መሆኑን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ከሰጠው ትዕዛዝ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት /መልስ ሰጭን/ ተጠሪን ሣይጠራ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት በመዝገብ ቁጥር 282882 ሰኔ 6 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ሰርዞታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ማጣሪያ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ የሚጣራ የሕግ ነጥብ የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 186600 መስከረም 7 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ዘግቶታል፡፡

2. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ሲከራከሩ፣ ጉዳዩ በይግባኝ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየ በኋላ ጉዳዩ ወደ አዳማ ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ፣ ጉዳዩ በሽማግሌ ዳኞች እንዲታይ ከአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤትና ከሀገር ሽማግለዎች በቀረበልን ሀሳብ መሰረት ሰባት ሽማግልዎች መርጠንና እነርሱ የሚወስኑትን ውሳኔ ለመቀበል ተስማምተን ሽማግሌዎቹ ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ሰጥተዋል በማለት በሰበር አቤቱታው ገፅ 2 የመጀመሪያው ፖራግራፍ የገለፀ ሲሆን፣ ተጠሪ የካቲት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው መልስ በተራ ቁጥር 9 ሁለተኛው ፖራግራፍ፣ እኔ ከአመልካች ጋር የነበረን የሁከት ክስ በሽምግልና ይለቅ የሚል ውል መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ከመፈረሜ ውጭ ያደረገሁት ሌላ ነገር የለም። የተመረጠ ሽማግሌ የለም በማለት ጉዳዩን በግልግል የሚያዩ ሽማግሌዎችን አልመረጥኩም በሚል ክርክር አቅርቧል። አመልካች መጋቢት 2 ቀን 2007 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የመልስ መልስ በሶስተኛው ገፅ 9 በተራ ቁጥር 9 ያሰፈረው ክርክር ቃል በቃል ሲነበብ "በአጠቃላይ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ የሽማግሌ ዳኞችን ውሳኔ በመቃወም መልስ የሰጡ ሲሆን ሽማግሌ ዳኛ አልሾምኩም ይበሉ እንጅ አመልካችና ተጠሪ በጋራ በመሆን መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሳኔ እንስማማለን በማለት ስንፈራረም የነበሩት ምስክሮች ራሳቸው ሽማግሌ ሆነው የውሳኔ ሀሳብ ሰጥተዋል" በማለት በመልስ መልስሳቸው ገልፀዋል።

3. ከዚህ ሰበር መዝገብ ጋር አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ያደረጉት ውል "በሽማግሌ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ለመገደድ በግራ ቀኙ ወገኖች የተደረሰ ስምምነት" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን ይዘቱም ቃል በቃል ሲነበብ "እኛ ስማችን ከላይ የተጠቀሰው ተዋዋይ ወገኖች በመካከላችን ስለተፈጠረው አለመግባባት በመረጥናቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት የሁለታችንንም ወገኖች ሀሳብ በመስማት የወከልናቸው ሽማግሌናዎች በጋራ ተወያይተው በሚሰጡት ውሳኔ የምንገደድ መሆኑን እየገለፅን የጉዳዩ ፍሬ ነገር በሽማግሌዎች ውይይት ላይ በቃለ ጉባኤ በሚገለፀው ጉዳይ በሚሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ወገኖች ወስደን ተግባራዊ ለማድረግ የምንገደድ ይሆናል" የሚል ይዘት ያለውና አመልካችና ተጠሪ የፈረሙበትንና "የታዛቢ ሽማግሌዎች ፊርማ" የሚል የስድስት ሰዎች ስም ዝርዝርና ፊርማ ያለበት ነው።

4. የሽማግሌ ዳኞች የሰጡት ውሳኔ መሆኑን ገልፆ አመልካች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአፈፃፀም ክሱ ጋር የያዘው የሰባት ሽማግሌዎች ስም የያዘው መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም "የአስታራቂ ሽማግለዎች ውሳኔ ቃለ ጉባኤ" የሚል ርዕስ ያለው ሰነድ ከዚህ ሰበር መዝገብ ጋር ተያይዟል። በሰነዱ፣ አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም ሲስማሙ፣ 1ኛ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ አወቀ አለማየሁ በተራ ቁጥር 2 የሽማግሌ ዳኛ ሆነው መሰየማቸውን፣ ሁለተኛ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ እንዳለ መንገሻ በ3ኛ ተራ ቁጥር የሽማግሌ ዳኛ ሆነው መሰየማቸውን፣ 3ኛ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ ተሊላ ቂንቢ በ4ኛ ተራ ቁጥር የሽማግሌ ዳኛ ሆነው መሰየማቸውን አምስተኛ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ ከበደ ዱሬሳ በ6ኛ ተራ ቁጥር የሽማግሌ ዳኛ ሆነው የተሰየሙ መሆኑን፣ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ ጀማል መሐመድ በ7ኛ ተራ ቁጥር የሽማግሌ ዳኛ ሆነው መሰየማቸውን፣ ታዛቢ ሽማግሌ ሆነው የፈረሙት አቶ በኪሪ አቡና በአምስተኛ ተጠራ ቁጥር የሽማግሌ ዳኛ ሆነው የተሰየሙ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ በተስማሙበት ሰነድ በሰብሳቢ የሽማግሌ ዳኝነት ወይም በታዛቢ ሽማግሌነት ስማቸው

ያልተገለፀው አቶ ጌታቸው ደበሌ በሰብሳቢ ዳኝነት የተሰየሙ መሆኑንና የሽማግሌ ዳኞች ውሳኔ በተባለው ሰነድ ላይ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ጉዳያቸውን በዕርቅ ለመጨረስ ሲስማሙ ታዛቢ ሽማግሌዎች የነበሩት አቶ በክሪ አቡና እና አቶ ጀማል መሐመድ ያልፈረሙበት መሆኑን አመልካችና ተጠሪ ስድስት ታዛቢ ሽማግሌዎች ባሉበት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲወስን መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተዋዋሉ የውል ሰነድና መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈውና በአምስት ሽማግሌዎች የተፈረመው የአስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ሰነድ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል።

5. ከላይ በዝርዝር ካሰፈርኩት የግራ ቀኙ ክርክርና መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት ውልና መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ከተፃፈው የአስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ሰነድ ከመረመሩ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት በእርግጥም የህግ መስፈርቱም አሟልቶ የተቋቋመ የግልግል ዳኞች ጉባኤ ያለ ስለመሆኑና የግልግል ጉባኤው የሰጠው ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ መኖሩን ተጨማሪ ማጣራት እንዲደረግና ዕውነታው እንዲረጋገጥ የሚያስገድድ ነው የሚል ዕምነት አለኝ። ለዚህም ምክንያቴ አመልካች ተጠሪ ጉዳያቸው በሽማግሌ ዳኞች እንዲያልቅ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ያደረጉት ውል፤ ውሉ ስለመደረጉ በታዛቢነት የፈረሙት ስድስት ሽማግሌዎች ጉዳዩን በሽማግሌ ዳኝነት አይተው እንዲወስኑ የተስማሙ መሆናቸውን በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ውሉ ታዛቢ ሽማግሌዎቹን የግልግል ዳኞች ሆነው እንዲያዩ የሰየምንበት ሰነድ ነው ሲል፤ ተጠሪ ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይ የተሰማማን መሆኑን የሚያረጋግጥ የውል ሰነድ እንጂ በታዛቢነት የፈረሙትን ስድስት ሽማግሌዎች የግልግል ዳኛ ሆነው የተሾሙበት የውል ሰነድ አይደለም ስለዚህ ጉዳዩን አይተው የሚወስኑ ሌሎች ሽማግሌዎች መምረጥ ነበረብን፣ አልመረጥንም፣ በማለት የሚከራከር በመሆኑ ነው።

6. አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ያደረጉት ውል በታዛቢነት /በምስክርነት/ በውሉ ላይ የፈረሙትን ሽማግሌዎች የግልግል ዳኛ ሆነው ጉዳዩን እንዲያዩ የተደረገ ነው ቢባል እንኳን አንድ ሌላ መጣራትና ግልፅ ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አለ። ይህም ጉዳዩን በሰብሳቢ ዳኝነት ያዩት አቶ ጌታቸው ደበሌ እንዴት እና በምን ሁኔታ ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ጉዳዩን አይተው ውሳኔ ሰጡበት የሚለው ነው። አቶ ጌታቸው ደበሌ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ባደረጉት የውል ሰነድ ላይ በታዛቢ ሽማግሌነት ስማቸው አልተገለፀም። በታዛቢ ሽማግሌነትም ፊርማቸውን አልፈረሙም። አቶ ጌታቸው ደበሌ፣ በውሉ ላይ በታዛቢነት ስማቸው የተገለፁትን ስድስት ሽማግሌዎች ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው እንዲሰሩ አመልካችና ተጠሪ በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 3332 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የመረጧቸው ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔና አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር አያሳይም። አቶ ጌታቸው ደበሌ በሰብሳቢነት መርጠው ያመጧቸው ስድስቱ ታዛቢ ሽማግሌዎች ስለመሆናቸው ወይም አቶ ጌታቸው ደበሌ ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ጉዳዩን እንዲያዩ በፍርድ ቤት የተሾሙ መሆኑንና በሌላ አነጋገር ሰብሳቢ ዳኛው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3332 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የተሰየሙ መሆኑን፣ አቶ ጌታቸው ደበሌ በሰብሳቢ ዳኝነት ተሰይመው መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ አያሳይም። ከዚህ አንፃር ሰብሳቢ ዳኛው በፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 3332 ንዑስ አንቀፅ 1፣ ወይም ንዑስ አንቀፅ 2 ወይም ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ጉዳዩን ለማየት

የተሰየሙ የግልግል ዳኛ መሆናቸውን ከግራ ቀኙ ክርክርና ከስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡

7. ሌላው ጥርጣሬ የሚፈጥረው ጉዳይ፣ አመልካችና ተጠሪ ጉዳያቸው በሽማግሌዎች ታይቶ እንዲወሰን መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ውል ሲዋዋሉ 5ኛ ተራ ቁጥር ታዛቢ ሆነው የፈረሙት አቶ ጀማል መሐመድና 6ኛ ተራ ቁጥር ታዛቢ ሆነው የፈረሙት አቶ በክሪ አቡና፣ በዚያው ቀን ማለትም መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ስማቸው በሰባተኛና አምስተኛ የሽማግሌ ዳኝነት ከተሰየመ በኋላ በውሳኔው ላይ ያልፈረሙ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ ሁለቱ ሽማግሌዎች በውሉ ላይ 18/07/2006 ዓ.ም ሲፈርሙ፣ በዚያው ቀን 18/07/2006 ዓ.ም የተሰጠው የሽማግሌዎች ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ሰነድ ላይ ሣይፈርሙ መቅረታቸው በእርግጥም፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3328/1/ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3331 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3332 ድንጋጌዎችን የሚያሟላ ሁኔታ የሽማግሌዎች የግልግል ጉባኤ እና የግልግል ጉባኤ ዳኛ ተቋቁሞ የሰጠው የፀናና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ አለ ወይስ የለም? የሚለው ጭብጥ ያልተጣራ መሆኑንና መጣራት የነበረበት መሆኑን ያሳያል፡፡

8. የፀናና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት የአፈፃፀም ክስ ያቀረበው ሰው መሆኑን የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 378 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሽማግሌ ግልግል ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ የአፈፃፀም ከሳሽ ጉዳዩ የሽማግሌ ግልግል ዳኞች እንዲታይ የተደረገበትን ስምምነት፣ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት አይተው የወሰኑት ዳኞች ሰብሳቢ ዳኛው ከፍርድ ባለዕዳው ጋር በተደረገው ስምምነት ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3331 እና ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3332 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ተሰይመው ውሳኔውን የሰጡ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ጉዳያቸው በግልግል ለመጨረስ 18/07/2006 ዓ.ም ውል ሲዋዋሉ በታዛቢነት /በምስክርነት/ የፈረሙት ሽማግሌዎች በምን ሁኔታ የግልግል ዳኛ ሆነው ተሰይመው ጉዳዩን አይተው እንደወሰኑና የግልግል ዳኞች ሰብሳቢ ሆኖ የተሰየመው አቶ ጌታቸው ደበሌ እንዴትና በማን የግልግል ዳኞች ሰብሳቢ ዳኛ ሆኖ እንደተሰየመ አመልካችና ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ያደረጉት ውልም ሆነ መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈውና በአምስት ሽማግሌዎች የተፈረመ ብቻ "የአስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ቃለ ጉባኤ ሰነድ" አያሳይም፡፡

9. ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ አይቶ ትዕዛዝ የሰጠው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3318 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3324 ባሉት ድንጋጌዎች የተዘረጋውን የዕርቅ ስርዓት፣ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3325 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3346 ከተዘረጋው የግልግል ዳኝነት ስርዓት ልዩነት ያላቸው መሆኑን ሳያገናዝብና ሣይረዳ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3345/1/ መሰረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል የፀና የግልግል ዳኞች ውሳኔ አለ ወይስ የለም የሚለውን ጭብጥ በጭብጥነት ይዞ ሣያጣራ፣ ዕርቅን መሰረት አድርጎ የአፈፃፀም ትዕዛዝ የሰጠ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት የሚከራከሩበት በሕግ አግባብ በተቋቋመ የግልግል ጉባኤ የተወሰነ የፀና ውሳኔ አለ ወይስ የለም የሚለው ጭብጥ ሣያጣራውና ውሳኔ ሣይሰጥበት ያለፈው መሆኑን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18118 ሚያዝያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ በመጀመሪያ የፀናና በፍርድ ቤት

ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል የግልግል ጉባኤ ውሳኔ አለ ተብሎ ከመደምደሙ በፊት በመጀመሪያ ከላይ የዘረዘርኳቸው ጭብጦች በማጣራት የስር ፍርድ ቤት እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/2/ መሰረት ጉዳዩ ሊመለስ ሲገባው፣ ይህ ሰበር ችሎት የፀናና ሊፈፀም የሚችል የግልግል ዳኞች ውሳኔ አለ ብሎ በደረሰበት መደምደሚያ የማልስማማ በመሆኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

10. ከላይ የግልግል ዳኞች እና የግልግል ዳኞች ሰብሳቢ በሕግ አግባብ የተሰየሙ ስለመሆናቸው ሊጣሩ ይገባቸዋል በማለት ያስቀመጥኳቸው የልዩነት ነጥቦች እንዳሉ ሆነው አብላጫው ድምፅ የግልግል ዳኞች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3325 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3346 እንደዚሁም ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 315 እስከ ፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 319 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 350 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 357 ያሉትን ድንጋጌዎች በጥቅል በመጥቀስ ውሳኔው የፀናና ሊፈፀም የሚችል ነው በማለት ከደረሰበት መደምደሚያ የምለይባቸው ተጨማሪ ምክንያቶች አሉኝ፣ ይኸውም ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ አመልካችና ተጠሪ ውል ሲዋዋሉ ምስክር የነበሩ ሰዎች እንዴትና በምን ሁኔታ የግልግል ዳኛ ሆነው እንደተሰየሙ የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች ማያቀርብና የግልግል ዳኛ ሰብሳቢ ሆኖ የተሰየመው ሰው አመልካች ተጠሪ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ሆኖ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3332 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ካልተረጋገጠ፣ መጀመሪያውኑም በሕግ አግባብ ያልተቋቋመና ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት አይተው እንዲወስኑ ስልጣን የሌላቸው ሰዎች ተሰባስበው ያዘጋጁትን ሰነድ መሰረት ያደረገ የአፈፃፀም ክስ ተጠሪ ሲቀርብለት፣ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የግልግል ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ባለመሆኑ እንዲፈፅም አልገደድም በማለት መቃወሚያ ከማቅረብና መቃወሚያውን የሚድግፍ ማስረጃዎች ከማቅረብ አልፎ፣ በሕግ አግባብ የተቋቋመው ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ እንዲሻርለት ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 380 እስከ ፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 354 ለተደነገገው ስርዓት ይግባኝ እንዲል የማይገደድ መሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 351 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 355 እስከ ፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 357 በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በሕግ አግባብ መቋቋሙ ያልተረጋገጠው የግልግል ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ ውድቅ እንዲደረግለት /SeTasid of Judgment/ የመጠየቅ ግዴታ በሕጉ ያልተጣለበት መሆኑን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 356 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል የሚል ሀሳብ ያለኝ በመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 350 እስከ ፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 357 ያሉት ድንጋጌዎች ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡

11. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት አይተው ወስነዋል ከተባሉት ሰባት ሰዎች ውስጥ የሁለቱ ሰዎች በውሳኔው ላይ አለመፈረም የማያስከትለውን ውጤት፣ በተመለከተ አብላጫው ድምፅ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የማልስማማበት ነጥብ አለ፡፡ ይኸውም የዘመድ ዳኝነት የሚከተለው ስነ ስርዓት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ የተደነገገ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ 3345/1/ የተደነገገ ሲሆን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀፅ 317 ንዑስ አንቀፅ 1 የግልግል ወይም የቤተዘመድ ጉባኤ የሽምግልና የዳኝነት ስራ አፈፃፀም ሁሉ በተቻለ መጠን በፍትሐበሔር ጉዳይ ከሚሰራበት ስነ ስርዓት ጋር ተመሳሳይና ተስማሚ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግልግል ዳኞች ከአንድ በላይ ከሆኑ በድምፅ ብልጫ ውሳኔ እንደሚሰጡ፣ የሽማግሌ ዳኞች ብይኑና ቀን፣ አመተ ምህረት ተሞልቶበት በአባሎቹ ከተፈረመ በኋላ ለተገልጋይ ወገኖች አንድ አንድ ግልባጭ የሚሰጣቸው መሆኑን

የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 318 ንዑስ አንቀፅ 3 እና ንዑስ አንቀፅ 4 ይደነግጋሉ፡፡ ይህም ሁሉም የግልግል ዳኞች በተገኙበት ጉዳዩ መታየት እንዳለበትና ጉዳዩ ሁሉም አይተው መወሰናቸውን ለማረጋገጥ ውሳኔው የተሰጠበት ቀን፣ ወርና አመተ ምህረት እንደዚሁም የግልግል ዳኞቹ ፊርማ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 318 ድንጋጌዎች በጠቅላላውና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 318 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ በልዩ ሁኔታ የሚያሳዩ መሆኑን ያመለክታል የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

12. ከዚህ ውሳኔው ላይ ሁሉም ዳኞች ስማቸው ብቻ ሣይሆን ጉዳዩ ሲታይ በአካል ተገኝተው የነበሩ ስለመሆኑ ሌላ ማረጋገጫ በሌለበት ሁኔታ ከግልግል ጉባኤ አካላት ሁለቱ አለመፈረማቸው ምን ውጤት ይኖረዋል? የሚለው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 317 ንዑስ አንቀፅ 1 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 318/4/ እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 183 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መመርመር ይጠይቃል፡፡ አመልካች ሁለቱ የግልግል ዳኞች ውሳኔው ሲሰጥ የነበሩ፣ በጉዳዩ የመከሩና አብረው የወሰኑ ስለመሆኑ የቀረበው ማረጋገጫ አለ ብሎ ለመደምደም የግልግል ጉባኤው 18/07/2006 የሰጠው ውሳኔ ይዘት በማየት ብቻ አያስችልም፡፡ አመልካች የግልግል ዳኞች ከአካባቢው ስለተለዩ ነው ያልፈረሙት ከሚል በስተቀር በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 317/1/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 183/2/ መሰረት የግልግል ዳኞች በሞት በዝውውር ወይም በሕመም ምክንያት ያልፈረሙ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ዳኞችም በውሳኔያቸው ይህንን በልዩ መግለጫ መልክ አስቀምጠው አልተፈራረሙበትም፡፡ ይህ ከሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 317/1/፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 318/4/ እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 183/2/ መሰረት በህግ ፊት ውጤት ያለውና የፀና ሁሉም የግልግል ጉባኤ ዳኞች ተሟልተው አይተው የሰጡትና በፊርማቸው ያረጋገጡት ውሳኔ የለም ተብሎ የአፈፃፀም ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል የሚል ሀሳብ ያለኝ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**